## የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)
## Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

### በ አውስትራለያ (ሜልበርን ከተማ) ስለተከሄደው ህዝባዊ ስብሰባ፤

### አጭር ዘገባ

**በሜልበርን ከተማ አውስትራሊያ የኢህአፓ ህዝባዊ ስብሰባ ተካሄደ።**

በ4/9/11 ከቀኑ 2፡00 ሰዓት ከሰዓት በኋላ የኢህአፓ ደጋፊዎችና ጥሪውን አክብረው የተገኙ ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን የተገኙበት ይህ ስብሰባ፤ በትግሉ የተሰዉትን ሰማ ዕታት በማስታወስና የህሊና ፀሎት በመድረግ ተጀመረ። ከዚም ከኢህአፓ የበላይ አመራር አባልና የ አህጉራዊ አመራር ኮሚቴ ጓዶች በየተራ ፤ ስለወቅቱ የሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ፣ ስለ ኢህአፓ ፖሊሲዎችና አቋሞች እንዲሁም በሀገር ቤትና በውጭ ድርጅቱ እያካሄደ ስላለው እንቅስቃሴ፤ ሰፊና ዝርዝር ማብራሪያ ከሰጡ በሁዋላ፣ ከተሰብሳቢ እንግዶች የቀረቡትን የተለያዩ ጥያቄዎችና አስተያየቶች በመቀበል፣ መልሶችና ማብራሪያዎችን ሰጥተዋል።

አብዛኛው ውይይትና ጥያቄዎች በግምባርና ትብብር ጉደዮች ላ ይ ያተኮረ ነበርናም ፤ በነዚህ ዓበይት ጉዳዮች ላይ የ ኢህአፓ አቋሞች ምን ምን እነደሆኑና ሲያደርጋቸው የቆየውንና አሁንም እያደረገ ያለውን እንቅስቃሴ በሰፊው በማብራራትና በመስረዳት ገላፃ ተደርጓል። ከዚህም በላይ በአሁኑ ወቅት ከወያኔው አሸባሪና አምባገነን አገዛዝ በተጨማሪ፣ የጠባብ ብሄርተኞች ና ደጋፊዎቻቸው በሀገራችን ህለውና ላይ ሊያስከትሉ የሚችሉትን አደጋ በመገንዘብ እያንዳንዱ ሀገር ዋዳድ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ለሀገሩ በቁርጠኝነት ዘብ እንዲቆምና ከአንድነት ሀይሎች በተለይም ከኢህአፓ ጋር አብሮ በመሰለፍ፤ ያለማወላወል እነዲታገልና የዜግነት ግዴታውን እነዲወጣ በማሳሰብ ፣ ለሁሉም ሀገርዋዳድ ዜጋ ድርጅቱ ያቀረበውን ጥሪ በድጋሚ አስተላልፏል።

**ሰብሰባውም በጥሩ መንፈስ ተካሂዶ ማምሻ ላይ ተጠናቅቋል።**

EPRP
P.O.Box 73337 Washington DC, 20056
USA

EPRP
BP 22
Bois Columbes 92270
France

Tel . 202-291-4217
Fax 202-291-7645
E-mail : ESPIC@aol.com
Website: http://www.EPRP.com